# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 24 ቀን 20/7/67

## አድሃሪ ማነው? ተራማጅስ?

'እስከዛሬ ድረስ ያለው ታሪክ የመደቦች ትግል ታሪክ ነው' ይላሉ የሶሻሊዝም አዛውንቶች ማርክስና ኤንግልስ::እውነትም ከዝቅተኛው የጋርዮሽ ዘመን ወዲህ የሰውን ልጅ ታሪክ ብንመረምረው በየትም አገር በማንኛውም ጊዜ አራማጅ ሞተሩ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙት መደቦች መካከል የሚደረገው ትግል ነው::ባርያ ፈንጋይ መደብ ከባርያ መደብ፡የባለርስት መደብ ከጪሰኛ፡ከበርቴው ከወዝ አደር፡ባጭሩ በዝባዥ ከተበዝባዥ ጋር ሲታገሉ ታሪክን ወደፊት እየገፉ አሁን ካለንበት ወቅት አድርሰውታል::በዚህ በማያቋርጥ ትግል የታሪክን የወደፊት እርምጃ ለመግታት /ዞሮ ዞሮ ሳይሳካላቸው/ የሚፍጨረጨሩት አድሃሪ መደቦች ናቸው::ከታሪክ ጋር እየተጋገዙ ለእርምጃና ለሰው ልጅ ደህንነት የሚታገሉት ደግሞ ተራማጅ መደቦች ናቸው::

እርምጃን የሚፈልጉና ለዚህም የሚታገሉትን መደቦች ለመምራት በታሪክ ፊት ሃላፊነት የወሰዱ ግንባር ቀደሞች የሰፊውን ሕዝብ ትግል በዚሁ በመደቦች ትግል አንፃር መመልከት አለባቸው:: ለዚህም በጠቅላላው የጊዜውን የአለም ሁኔታና በተለይ ደግሞ በሚገኙበት ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን የመደቦች አሰላለፍ በጥንቃቄ ማጥናት ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው::ይህንንም የሚያደርጉበት ዋናው ምክንያት ማንኛው መደብ የረቮሉሽኑ ተፃራሪና አድሃሪ መደብ እንደሆነ፡የትኛው መደብ ደግሞ የረቮሉሽኑ ደጋፊና ተራማጅ መደብ እንደሆነ ተገንዝበው ወዳጅን ከጠላት ለመለየት እንዲችሉ ነው::ባለፈው 'የሰፊው ሕዝብ ድምጽ' እትማችን እንዳመለከትነው በዚህ መልክ ወዳጅና ጠላትን የለየው ረቮሉሽን ደጋፊዎችን መሰብሰብ ማደራጀትና ለትግሉ ማጠናከር፡ጠላቶችን ደግሞ መከፋፈል መበተንና ማድከም ማንኛውምከግቡ የደረሰ ረቮሉሽን የተከተለው የትግል አቅድ ነው:: የኛም ረቮሉሽን ከዚህ የተለየ ጐዳና ሊከተል አይችልም::

በመጋቢት 7 ቀን 1967 ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት 'አድሃሪ ማነው? ተራማጅስ' በሚል አርእስት መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል::የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ወዳጅና ጠላት መደቦች በሚገባ ተለይተው ትግሉ ወደፊት ሊራመድ ነው ብለን ጓጉተን ነበር::ነገር ግን ተስፋችን ከንቱ ሆኖ ቀርቷል::የቀረበው ትንተና ጊዜንና አካባቢን የሳተ ብቻ ሳይሆን የመደብ ትንተና ይዘትም ስለሌለው ለሰፊው ሕዝብ ምንም አይነት የረባ ትምህርት ሳይሰጥ ቀርቷል::የአንድን ረቮሉሽን ወዳጅና ጠላት ለመለየት ተነስቶ አድሃሪ <u>መደቦች</u> እነማን እንደሆኑ፡ተራማጅ <u>መደቦችስ</u> እነማን እንደሆኑ አለማውሳት ምን ይዞ ጉዞ ይሆናል::ይህም ትንተና ሳይንስን የተመረኮዘ ባለመሆኑ በሰው መንፈስ ውዥንብር ስለሚነዛ እንቅፋትነቱ ያመዝናል::

መግለጫው አንድ አድሃሪ <u>ግለሰብ</u> ወይም አንድ ተራማጅ <u>ግለሰብ</u> ምን ምን አይነት ጠባዮችና ዝንባሌዎች ሊኖራቸው እንደሚችል ከማስገንዘብ አያልፍም::አድሃሪ ማለት ርኩስ፡አወናባጅ፡ተንኮለኛ፡ደካማ ፍጡር፡ድንጉጥ፡የነጋበት ያፈና ጅብ ... ማለት ነው ይላል::ተራማጁንም እንደዚሁ ግለሰባዊ ዝንባሌዎችን በሚመለከቱ ቅጽሎች ለመግለጽ ይሞክራል::እርግጥ ነው፡አድሃሪ መደቦች ከህብረተሰቡ ጥቅም የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ ስለሆኑ የታሪክን እርምጃ ለመቋቋም በሚያደርጉት ትግል የተጠቀሱት ዝንባሌዎች ሊኖሯቸው ይችላሉ፤ አሉአቸውም::ተራማጆችም የተጠቀሱት የሕዝብ ፍቅር፡የመስዋእትነት፡የጀግንነት ዝንባሌ አላቸው::ግን ይህ የግለሰቦች ዝንባሌ፡ከሚገኙበት ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው::ይህ በግልጽ መታወቅ አለበት::ላይ ላዩን ሲመለከቱአቸው ሰው አክባሪ፡እግዚአብሄርን ፈሪ፡ደግና ርህሩህ የሚመስሉት የመንደር አዛውንት በመደብ ትግል

አንፃር ሲመጡባቸው እልም ያሉ አድሃሪያች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመንደሩ በተመሰከረላቸው ግለሰባዊ ቅምነገረኛነት የተጭበረበረ ተበዝባዥ፡ የመደብ ትግልን ተቀዳሚነት ያልተገነዘበ ተበዝባዥ፡ በእነኝህ አድሃሪ አዛውንት ሊወናበድ ይችላል ማለት ነው፡፡

በኛ ግምት የኢትዮጵያን ሪቮሉሽን ወዳጅና ጠላት ለመለየት ከግለሰባዊ ዝንባሌያች አልፈን አድሃሪ መደብ ማን እንደሆነ፡ ተራማጁስ መደብ ማን እንደሆነ ማየትና ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሆኖ በደፈናው አድሃሪ መደብ ወይም ተራማጅ መደብ ብሎ መናገር ችግር ነው፡፡ የመደቦች አሰላለፍ በሚጠናበት ጊዜ ህብረተሰቡንና ታሪካዊ ወቅቱን ለይቶ ማመልከት ፈጽሞ ሊዘለል የማይቻል ሃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ሪቮሉሽናችንን ለማራመድ መጠየቅና መመለስ ያለብን ዛሬ በ1967 ኢትዮጵያ አድሃሪ መደብ ማነው፡ ተራማጁ መደብስ ማነው የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ከሁሉ በፊት አገሪቱ የምትገኝበትን የእድገት ደረጃ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬም ቢሆን ገና ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም የጭቆናና የበዝበዛ ቀንበር ያልተላቀቀች አገር ነች፡፡ በዚች ምድር ላይ በአሁኑ ወቅት ሊደረግ የሚችለው ሪቮሉሽን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ስለሆነ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ወይም ደግሞ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ነው፡፡ በዚህም አብዮት የሪቮሉሽኑ አላማ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ከኢትዮጵያ ገጸ አጥፍቶ በነርሱ መቃብር ላይ አዲሲቱዋን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በመመስረት ለሶሻሊዝም ጥርጊያ ጎዳናውን መክፈት ይሆናል፡፡

እንግዲህ በዚህ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በአንድ በኩል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና አጋዞቹ በሌላ በኩል የተሰለፉበት ትግል በዝርዝር መልኩ መታየት አለበት፡፡ ባለፈው ቁጥራችን እንዳመለከትነው የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ የወጣው አዋጁ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የመደቦች አሰላለፍ የተጣራ መልክ ይሰጠዋል፡፡ በአድሃሪ መደቦች በኩል መሳፍንት፡ መኳንንት፡ ታላላቅ ጳጳሳት፡ ታላላቅ ነፍጠኞች፡ የሰሜንም ሆነ የደቡብ ክፍል ተወላጅ የሆኑ ታላላቅ ባላባቶች፡ ኢምፔሪያሊስቶችና ቡችሎቻቸው አቀባባይ ከበርቴያች፡ ከፍተኛ የቢሮ ከበርቴው፡ የፖለቲካ ሃይሉ ኢምንት ቢሆንም በቀርቡ የተወረሰው ብሄራዊ ከበርቴ፡ ገና ከአሁኑ ለውጡ ርቆ የሄደበት የንኡስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍና በጠቅላላው የነዚህ አድሃሪ መደቦች አጫፋሪያችና ርዝራዦች ናቸው፡፡ እነዚህ ዛሬ የሪቮሉሽኑ ጠላቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተራማጅ መደቦች በኩል ወዝአደሩ፡ ከመሬታቸው ላይ የተነቀሉና የባለመሬት ጭቆና ያቀረቀዛቸው ጪሰኞች፡ መለስተኛና ድሃ ገበሬያች፡ ምሁሩ፡ ተማሪው፡ የወታደሩ ተራማጅ ክፍል፡ ትናንሹ ነጋዴና ዝቅተኛው የመንግስት ሰራተኛ፡ ከጪሰኛው ባልተሻለ ኑሮ የሚማቅቁት ዝቅተኛ ቀሳውስት....እነዚህ ሁሉ በአሁኑ ወቅት የሪቮሉሽኑ ደጋፊያች ናቸው፡፡

በነዚህ ወዳጅና ጠላት መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚወላውሉና አንዴ ወደአንዱ አንዴ ደግሞ ወደሌላው እያዘነበሉ አንጠበጥ የሚሉ ሃይሎች አሉ፡፡ እነዚህ በመሰረቱ እድገታቸው በመሳፍንቱ ስርአትና በኢምፔሪያሊዝም ታፍኖ የቀረቀዘባቸው፡ እስካሁንም የተደረገው ለውጥ በቀጥታ ያልመታቸው የብሄራዊ ከበርቴውና የንኡስ ከበርቴው ታዳጊ ክንፎች ናቸው፡፡ እድገታቸውን ስለሚያደናቅፉባቸው ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ ለመሳተፍ ይፈልጋሉ፡፡ ግን ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ መደባዊ አቀማመጣቸው በመጠኑም ቢሆን ከበዝባዥ ወገን ስለሚያሰልፋቸው የሰፊውን ሕዝብ ንቅናቄ በሙሉ ልብ ለመደገፍ ይፈራሉ፡፡ በማንኛውም ሪቮሉሽናዊ ትግል እንደታየው ቁርጠኛ የሆኑት የሪቮሉሽኑ ጠላቶችና ደጋፊያች የሚያደርጉት ትንንቅ ጣምራ መልክ አለው፡፡ በአንድ በኩል ራሳቸውን ለማደራጀትና ለወሳኙ ትግል ሃይላቸውን ለማጠናከር አጥብቀው ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ እነዚህን መሃል ሰፋሪ የሆኑ ሃይሎች በማረጋጋትና በማግባባት ለመሳብና በአጋዥነት ለማሰለፍ ይጥራሉ፡፡

በበኩላችን የሪቮሉሽኑን ቁርጠኛ ደጋፊያች የማደራጀቱን ጉዳይና ለዚህም ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እንደህይወት አስተንፋስ የሚያስፈልጉት መሆኑን ባለፈው እትማችን አስገንዝበናል፡፡ አሁንም ቢሆን ለመደራጀት በሚደረገው ጥረት የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች እንዳይቀድሙን በጣም መትጋት ያስፈልጋል፡፡

እዚህ ላይ ለማተኮር የምንፈልገው ጉዳዩ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ቢሆንም መሃል ሰፋሪዎችን ወደሬቮሉሽናችን የመሳቡን ጉዳይ ነው:: ነገሩ ግልጽ ነው:: አሁን እንደሚታየው ከሆነ የደርጉ ያልተጣራ ፖለቲካ የብሄራዊ ከበርቴውን ተራማጅ ክንፍና ንኡስ ከበርቴውን ወደፀረሬቮሉሽኑ ሰፈር ወርውሮአቸዋል:: በዚህ በኩል በሚደረገው ትግል አድሃሪ ሃይሎች ከመጠን በላይ በመፍጨርጨር ላይ ናቸው:: ሬቮሉሽኑን በተቻለ መጠን ለማስጠላትና ተራማጆችን ለመነጠል: በዚህም መሃል ሰፋሪውን ሁሉ ወደነርሱው አደባልቀው ሃይላቸውን ለማዳበር ይጥራሉ:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆን በመላ አለም የሲአይኤ ቡችሎች የሰለጠኑበት በወሬና በፕሮፓጋንዳ ሰውን የማስከር ዘዴ አለ:: በቅርቡ 'የኢትዮጵያ ዱል በኮሙኒስት ትግል' የሚል በነዚህ ቡችሎች የተበተነው ፀረኮሙኒስትና ፀረተራማጅ ጽሁፍ አድሃሪያቹ ይህንን በመላ አለም እጅ እጅ ብሎ የተጣለውን ጥንብ የትግል ዘዴ ወደሃገራችን ማስገባታቸውን ያሳያል:: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በስንት መከራና ስቃይ ከዚህ ደረጃ ያደረሰውን የነፃነት ትግሉን በዚህ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ይፈታዋል ብሎ ማለም የአድሃሪዎቹን ደደብነት የሚጠይቅ ቅዠት ነው:: ጽሁፉ የሚመክረው ምንድነው? በአሁኑ ወቀት ከመሃል ሆነው የሚወላወሉትን ሃይሎች አስፈራርቶና አወናብዶ ወደአድሃሪው ሰፈር ለማፈናቀል ነው:: እንደዚህም ስለሆነ ይህ 'ኮሙኒስት ነኝ' የሚለው ፀረኮሙኒስትና የሲአይኤ ቡችሎች ጽሁፍ 'ጠላት ናቸው እናጥፋቸው' የሚሉቸው ሃይሎች ቄሱን: ሸሁን: ከሁለት መቶ ብር በላይ ገቢ ያለውን ማናቸውንም ኢትዮጵያዊ: ከሩብ ጋሻ በላይ ያለውን ባለርስት: [illegible] ....እየጠቀሰ ነው:: እና ቁርጠኛ የሬቮሉሽናችን ጠላቶች የምንላቸውን መደቦች ፈጽሞ አያነሳቸውም::

የሆነ ሆኖ ደርጉ የሬቮሉሽናችንን ዋና ጠላቶች ለይቶ ለማሳየትና እነርሱንም ነጥሎ ለመምታት እንዲቻል ጊዜያዊም ቢሆኑ ሊገኙ የሚችሉትን ደጋፊዎች ለመሰብሰብ የሚያደርገው ጥረት ፈጽሞ ጥራት የለውም:: ስለዚህ አድሃሪዎቹና ቡችሎቻቸው እነዚህን ሃይሎች በፀረሬቮሉሽናዊ ፕሮፓጋንዳቸው አስክረው እንዲስቡአቸው ሰፊ የማወናበጃ መድረክ ሰጥቶአቸዋል:: ከላይ እንዳልነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በዚህ ርካሽ ማወናበጃ ይፈታል የሚል እምነት የለንም:: ነገር ግን በዚህ አቀጣጪ ግልጽ የሆነ ፖለቲካ ሲጠፋ ትግሉ ለጊዜውም ቢሆን ሊደናቀፍ ይችላል::

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ወደፊት ሊራመድ የሚችለው ዋና ጠላቶቹን ነጥሎ በመምታት ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉትን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በሙሉ ሰብስቦና አደራጅቶ ለትግል ያሰለፈ እንደሆነ ብቻ ነው:: ከዚህ አልፎ ተርፎ የትግሉ መሪ የሆነው ወዛደርና የትግሉ ምሰሶ ገበሬ ገና በሚገባ ባልተደራጁበት ወቀት ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ሌላ ተጨማሪ ጠላት ማፍራት ሬቮሉሽናችንን አደጋ ላይ ይጥለዋል::

የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል ይባላል:: ወዳጅና ጠላትን በተጣራ ሁኔታ አለለየንም:: በተወናበደ ፖለቲካ ወደአድሃሪው ሰፈር በመደባለቅ ላይ ያለውን ንኡስ ከበርቴና እንዲሁም ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለውን የብሄራዊ ከበርቴ ተራማጅ ክንፍ አርቀን እንጀገና የሬቮሉሽናችን ደመኛ ከሆነው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር የመታረቀ ፖለቲካ እንዳይሰፍን ያሰጋል:: ወዳጅና ጠላት በጊዜ ካልተለዩ ሬቮሉሽናችን ከትልቅ አደጋ ላይ ይወድቃል: ፀረኢምፔሪያሊስት መልኩን ይስታል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ለጊዜውም ቢሆን የአድሃሪዎችን እንደገና ማንሰራራት እንደሚያስከትል ማንም አይስተውም::

ዛሬ እነዚህን ወላዋይ ሃይሎች ለማረጋጋት አለመሞከርና ዝም ብሎ በነሲአይኤ አስካሪ ፕሮፓጋንዳ እንዲወናበዱ መልቀቅ ሁለት የተያያዙ አደጋዎችን ያመጣል:: የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮቻችን ከመጠን በላይ ሊባባሱ ይችላሉ::

በኢኮኖሚው በኩል የሄድን እንደሆነ ተራማጁ የብሄራዊ ከበርቴ ክንፍና ንኡስ ከበርቴው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ እያፈራረሰ በመጣል ላይ ካለው ከፊውዳሉ ስርአት ጋር ሲነፃፀሩ ተራማጅ አምራቾች ናቸው:: አገራቸውን ሸጠው ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ከተቆራኙት አቀባባይ ከበርቴዎች ጋር ሲነፃፀሩ እንደነሱ የሃገሪቱን ሃብት በትርፍ ስም እየዛቀ ወደውጭ በማጋዝ ኢኮኖሚውን የሚያቀረቁዙ ሃይሎች አይደሉም:: ባጭሩ በአሁኑ ጊዜ ከደመኛ ጠላቶቻችን ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ሲተያዩ እነዚህ ሃይሎች እነሱም በዛም ለጊዜው ከተራማጅ ሃይሎች ጋር ሊደመሩ ይችላሉ:: እንደዚህም

ስለሆነ ቀደም ተከተለን በሳተ ፖለቲካ፡ለምሳሌ ፈጽሞ አድሃሪ የሆኑትን የኢምፔሪያሊስት ወኪሎችና የኢኮኖሚያችንን አውራ ቋዦች በጠቀላላው ቁጥጥር ስር ሳያደርጉ፡ለጊዜውም ቢሆን ተራማጅ የሆኑትን ሃይሎች ለመምታት መሞከር የኢኮኖሚያችንን ከመጠን በላይ መዝረክረክ ያስከትላል፡፡ይህ ደግሞ ሪቮሉሽናችንን ለጊዜው ከአቅሙ በላይ ከሆነ የፖለቲካ ችግር ውስጥ ይከተዋል፡፡

የፖለቲካው ችግር የጠላቶች ከመጠን በላይ መብዛት የሚያመጣው ችግር ነው፡፡ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና .በዲሞክራሲ መንገድ የመደራጀት፡የመናገር፡የመሰብሰብ መብቱ ይመለስለኝ፤ በገዛ ሃገሩ አንገብጋቢ ችግሮች ላይ ባልፈራ ሳልገላመጥ ሃሳቤን የመስጠት ሰብአዊና ብሄራዊ መብቴ ይከበርልኝ እያለ እሪታውን በማሰማት ላይ ነው፡፡ይህ ጥሪ ሳይመለስ የምታልፈው እያንዳንዷ ቀን ለአድሃሪያቹ የወራት ፋታ ትሰጣቸዋለች፡፡በእንዲህ አይነቱ አስጊ ሁኔታ ላይ እያለን ዛሬ ለኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ሳይንሳዊ ትንተናና ወቅቱ ከሚፈቅዱለት ጠላቶች በላይ፡ከዋና ጠላቶቹ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ሌላ ተጨማሪ ጠላቶች ማጋፈጥ የመጨረሻ ድላችንን ቀን ማራዘም ነው፡፡ከላይ እንዳልነው በዚህ የፖለቲካ ውዥንብር ውስጥ ወዳጅ ከጠላት ተደበላልቆ ለኢምፔሪያሊስቶች በመዘጋት ላይ ያለው በር ተበርግዶ እንዳይከፈት ያሰጋል፡፡ይህ ከሆነ፡የኢትዮጵያ አብዮት ምን አይነት ውጥንቅጥ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል በኢንዶኔዥያና በቺሊ የተፈፀመውን የኢምፔሪያሊስቶች ግፍ፡እንዲሁም ሌሎች የኢምፔሪያሊስቶች ሴራ ለጊዜው ያከሸፋቸው ሕዝባዊ ትግሎች የወደቁበትን መከራ መመልከት ብቻ ይበቃል፡፡ስለዚህ በታሪክ ፊት ሃላፊነታችንን ወስደን ካሁኑ ቁርጠኛ የሆኑት ወዳጆችና ጠላቶች እ[illegible]ለዩ፤ መሃል ሰፋሪና ወላዋይ መደቦች ወደሪቮሉሽኑ ተደባልቀው እንዲረጋጉ፤ ለማንኛውም ደግሞ የነፃነቱ ትግል ባለቤትና ወሳኝ ሃይል የሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባስቸኳይ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ሳንሰለች አንወተውታለን፡፡የኢትዮጵያም ተራማጆች በሙሉ አንድነታቸውን ከብረት አጠንክረው በተጣራ መስመር ወደፊት እንዲራመዱ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

በየአቅጣጫው ዛሬ የተጣራ ፖለቲካ ይጠየቃል፡፡በዛሬው ወቅት የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋናና ደመኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ናቸው፡፡

የፊውዳሉን ስርአት በሚመለከተው በኩል 'መሬት ላራሹ' መታወጁ፤ የኢትዮጵያ አርሶአደር ሕዝብ በመደቡ ተሰልፎ እንዲደራጅ መታገዙ ለሪቮሉሽናችን አንድ የድል ዋስትና ነው፤ የተጣራ ፖለቲካ ነው፡፡ነገር ግን ይበልጥ መጣራት አለበት፡፡አወናባጅ የሲአይኤ ቡችሎች ጽሁፍ እንደሚለው 'መሬት ላራሹ' ሲባል፡የመሬት ይዞታ ከሩብ ጋሻ አይበልጥ ሲባል፡ከሩብ ጋሻ በላይ ያለው ሁሉ፡ግማሽም ጋሻ፡አንድም ጋሻ፡ሁለትም ጋሻ የሚያርሰው ባለርስት ሁሉ የሪቮሉሽኑ ደመኛ ጠላት አይደለም፡፡እንዲያውም ይህ ባለርስት በተወሰነለት ይዞታ ላይ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቢያርስ አዲሱ ሪቮሉሽናዊ ፖለቲካ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያተርፈው ፀጋ እሱንም ከቀረቀዘ ኑሮው ሊያላ[illegible]ው እንደሚችል ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡በሃገራችን መንደሮች ትምህርት ቤቶች ቢከፈቱ፡በጨለማ ለኖረው ለርሱም ልጅ የእውቀት በር እንደሚከፈትለት መነገር አለበት፡፡የጤና ጣቢያዎች ቢከፈቱ ለዘመናት ከተቆራኙት በሽታዎች እርሱም ሆነ ቤተሰቡ እንደሚፈወሱ እንዲያውቀው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ባጭሩ ንግድ፡ትምህርት፡ጤና፡ማመላለሻ ... ቢስፋፋ ከዚህ ሁሉ ብልጽግና ይህም ጉስቁላ ባለርስት ሰርቶ ተገቢ ድርሻውን ሊያገኝ እንደሚችል ተገልጦለት የሪቮሉሽኑ ደጋፊ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ፀረኢምፔሪያሊስት ትግላችንን በሚመለከተው በኩል የተጣራ ፖለቲካ ሲባል በቀዳሚያ በማያወላውልና ምንም አይነት ወለም ዘለም በሌለበት ሁኔታ የሃገራችንን ኢኮኖሚ ከባእድ ቁጥጥር ስር ጨርሶ ማላቀቅ ያስፈልጋል፡፡ባንኮችና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ብቻ ሳይሆኑ በባእዳን ቁጥጥር ስር ሆነው በትርፍ ስም የሚዝቁትን ሃብት ወደባህር ማዶ የሚያሻግሩትና የሃገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያቀረቅዙት የኢምፔሪያሊስቶች የንግድ እርሻዎች፡ፋብሪካዎችና እንዱስትሪዎች በሙሉ መወረስ አለባቸው፡፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ለኢምፔሪያሊስቶችና ለነርሱ ገበያ ታዛዥ እንዳይሆን የውጭ ንግድ፡የአስመጭና ላኪ ተግባር የመንግስት ሞኖፖል መሆን ይገባዋል፡፡

ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት የሆነው ትግላችን ተቀነባብሮ ለሃገሪቱ ጠቅላላ እድገት እንዲያተርፍ ኢኮኖሚያችን በአንድ ማእከላዊና አጠቃላይ ፕላን መመራት ይኖርበታል::

የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ጠንቅ ከሃገራችን መንግሎ ለመጣል እነዚህ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው::ይህ ስለሆነም በተለይ አሁን እንደሚደረገው በኢምፔሪያሊስቶች ላይ ወለም ዘለም የሚል ፖለቲካ መከተል ትግላችንን ፀረኢምፔሪያሊስትና የብሄራዊ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን መልኩን ያስተዋል::ይህንንም አጥብቀው ሳይይዙ ወደሶሻሊዝም መንጠራራት የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደሚባለው ይሆናል::

የተጣራ ፖለቲካ የምንለው ቁርጠኛ ጠላቶችን ግልጥልጥ አድርጎ ለይቶ ለነርሱ መጥፊያ እርምጃዎች-ከመውሰድ አይመለስም::ሬቮሉሽናችን በአሁኑ ጊዜ በፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ጥቅማቸው /ለጊዜውም ቢሆን/ የሬቮሉሽኑ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉትን ሃይሎች በጥንቃቄ መያዝና ወደሬቮሉሽኑ መሳብ ይገባዋል::ታላቁ ሌኒን በዚህ በኩል የሚሰጠን ትምህርት በማያዳግም ሁኔታ ግልጥ ነው:: በሱ ግምት ተራማጆች አጋዥን ለመሰብሰብ የአጋጣሚ ፍንጭ እንኳን መዝለል የለባቸውም::ይህንንም አጋዥ ጊዜያዊ ነው ብሎ መተው፣ ወላዋይና ቀንጥንጥ ነው ብሎ መናቅ፣ አያስተማምንም ብሎ ቸላ ማለት ሬቮሉሽናዊ የትግል ስልት አይደለም::በዋናው ጠላትና በሬቮሉሽኑ መካከል የሚወላውል ሃይል ሲሆን ጥቅሙን አሳይቶ ማረጋጋት የግንባር ቀደሙ ተግባር ነው::የማያስተማምን ከሆነ ራሱ በሬቮሉሽኑ እምነት ማጣቱ ነውና በተጣራ ፖለቲካ እምነት እንዲያድርበት ማድረግ የትግሉ አመራር ሃላፊነት ነው::

በኛ ግምት በነዚህ መሃል ሰፋሪና ወላዋይ ሃይሎች ላይ የሬቮሉሽኑ ፖለቲካ በሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይችላል::በመጀመሪያ ደረጃ መቼስ እነዚህ ሃይሎች ከሕዝቡ ጉን ተሰልፈው ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመውጋት ፈቃደኞች እስከሆኑ ድረስ የሬቮሉሽኑ ወዳጆች መሆናቸው መታወቅ፡መታወጅ፡ መለፈፍ አለበት::ሁለተኛ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ የንግድ ስራዎች፡ትናንሽ እንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች፡በትራንስፖርት፡በሆቴል ....የተሰማሩት የብሄራዊ ከበርቴው ተራማጅ ክፍሎችና ንኡስ ከበርቴዎች ሰርተው ተገቢ ጥቅማቸውን ሊያገኙ የሚችሉባቸው መስኮች ተጣርተው ሊብራሩ ይገባል:: እንደዚሁም ከተለየላቸው በሃላ ለነሲአፀኤ የሽብር ዘመቻ እንዳይመቹ በየሙያቸው ተደራጅተው ዋስትና ያለው ኑሮ ሊኖሩ ይገባል::ይህም ሆኖ በነዚህ በሚሰማሩባቸው መስኮች የህብረተሰቡንም ጠቅላላ ጥቅም እንዳያዛንፉ መንግስት ቁጥጥር ሊያደርግባቸው ይገባል::

በመጨረሻም ልንጠቅሰው የምንወደው ነገር አለ::የኢትዮጵያን ሬቮሉሽን እድል የሚወስነው ሃይል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው::ይህም ማለት ከሁሉ አስቀድሞ ወዝአደሩና አርሶአደሩ ማለት ነው::እንደዚሁም ስለሆነ የብሄራዊ ከበርቴው ተራማጅ ክንፍና ንኡስ ከበርቴው ባላቸው ሃይል ወደ ጠላቶቻችን ከሚደረቡ ይልቅ ወደሬቮሉሽኑ ይደባለቁ ብንልም እነዚህ ሃይሎች በምንም አይነት ከአጋዥነት ደረጃ ሊያልፉ አይችሉም፣ አይገባቸውምም::የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ዋናው አመራሩ በቁርጠኞቹ ሬቮሉሽናዊ መደቦች በተለይም በወዝአደሩ መያዝ ይኖርበታል::ለዚህም የኢትዮጵያ ወዝአደር መደብ ከሌሎቹ ሁሉ ይበልጥ ተደራጅቶና በትግሉም ውስጥ ግንባርቀደምነቱን አስመስክሮ የአመራሩን ችቦ መያዝ ይኖርበታል::

ኢምፔሪያሊስቶችን በመሰለ የአለም ሕዝቦች ቋሚና ዋና ጠላት ላይ የተድበሰበሰ አቋም ሲወሰድ እየተመለከቱ፣ ትግላችን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ መልኩን ስቶ ባልተጣራ ፖለቲካ ወዳጅ ከጠላት ሲደበላለቅ እያዩ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች በምንም አይነት ዝም አይሉም::ቋሚ ጠላት ተነጥሎ እንዲጠቃ፣ ጊዜያዊ ወዳጅ ከሬቮሉሽኑ እንዲደባለቅ፣ የሬቮሉሽኑ ባለቤት የሆነው ሰፊው ሕዝብ ተደራጅቶ በትግሉ ውስጥ ተገቢ ድርሻውን እንዲወጣ በሚደረገው ትግል ምንም አይነት አድርባይነት ባያወናብዳቸው ወደፊት መራመድ አለባቸው::

## የሲ. አይ.ኤ ስራ

'ጨለማ የለበሱ ሃሳዊ መሲሆች' በሚል አርእስት ስር መጋቢት 15 ቀን ከጊዜያዊው ወታ
ደራዊ መንግስት አንድ ሰፊ መግለጫ ወጥቶ እንደነበር ይታወሳል::ይህ መግለጫ የሚመለከተው 'የኢ
ት.ዮጵያ ድል በኮሙኒስት ትግል' በሚል ርእስ ስር ተጽፎ የተበተነውን አንድ ተንኮለኛ ጽሁፍ ነው::
አንድ ሰው ሙሉ ጽሁፉን ሳያነብበም እንኳን:የወታደራዊው መንግስት መግለጫ ከሚጠቀሳቸው ጥቂት አረ
ፍተነገሮች ብቻ ለመረዳት የምንችለው አንድ ነገር አለ::ይሸውም:የተባለው ጽሁፍ በፍፁም የእውነ
ተኛ ኮሙኒስቶች ስራ ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው::ማንኛውም የኢትዮጵያ ኮሙኒስት:ማንኛውም ተራ
ማጅ:ማንኛውም ቀን አሳቢ ሰው የዚህን አይነት ጽሁፍ አዘጋጅቶ እንደማይበትን ሳይታለም የተፈታ
ነው::ስራው በማያጠራጥር አኳሃን ያሜሪካኑ የስለላ ድርጅት የሲአይኤ ስራ ነው::
የጽሁፉ ዋና አላማ የመንግስቱ መግለጫ እንደሚለው 'ወታደሩን ከወታደሩ:ሕዝቡን ከሕዝብ:
አርስበርስ ለማጋጨት' አይደለም::የጽሁፉ ዋናና የመጀመሪያ አላማ ኮሙኒዝምን እንደጭራቅ ማስፈራ
ሪያ አድርጉ ለማቀረብና ደርጉን እራሱን ደግሞ በዚያው ኮሙኒስት ለማሰኘት ነው::ወታደራዊው መን
ግስት ህብረተሰባዊነትን ካወጀ ወዲህ:በኢምፔሪያሊስት ጋዜጦች 'ኮሙኒስት ነው' ተብሎ ሲወራበት
ቆይቶአል::አንዳንድ የምእራብ ጋዜጠችማ የደርጉን አባሎች ስም ጭምር እየጠቀሱ አገሌ ማርክሲስት
ነው ብለው ደጋግመው ጽፈዋል::አሁን ወታደራዊው መንግስት መግለጫ ያወጣበት ጽሁፍ በኛ ግምት ያተ
ስነዘረው ኮሙኒዝምንና ደርጉን አንድ አድርጎ ሁለቱንም በማስጠላት የዚህኛውን የመገለበጫ ሁኔታ
ለማዘጋጀት ነው::ይህም በብዙ አገሮች ተደጋግሞ የተሰራበት የታወቀ የሲአይኤ ዘዴ ነው::
በዚህ ሁኔታ:መንግስቱ ያወጣው መግለጫ ፈጽሞ አላማውን ስቶአል ማለት ነው::ነገሩ ከሁ
ለት አንዱ ነው::ወይ ወታደራዊው መንግስት ይህ ጽሁፍ የያንኪዎች ስራ መሆኑን ተገንዝቦታል፤
ግን ለችን በስሙ አልጠራውም::ወይንም ደግሞ ነገሩ የመጣው በርግጥ ከኢትዮጵያ ኮሙኒስቶች ነው
ብሎ አስቦአል::ይህም ከሆነ መንግስቱ በኢምፔሪያሊስቶች ስራ ላይ የመንቃት ችሎታ የለውም ማለት
ነው::ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት የተባለው ወረቀት የተንኮለኞችና የአድሃሪዎች:የሰላዮች ስራ
መሆኑን ካወቀ ለምን ለችን በስሙ ጠርቶ በተጣራና በማያሻማ ቋንቋ እነዚህን አላጋለጣቸውም? ወደ
ፊት መንግስቱ በሌሎች ወረቀት በሚበትኑ ተራማጆች ላይ ለመውሰድ የሚያስበው እርምጃ ኑሮት ያንን
ለመሸፈኛ ይህ ጥሩ አጋጣሚ መስሎት ይሆን? ማንም እንደሚያውቀው በአሁኑ ጊዜ ይህ ጋዜጣችንና
ሌሎችም እንደዲሞክራሲያ:እንደአብዮት ያሉት ነፃና ተራማጅ ጋዜጦች የሚሰራጩት በሸሸግ ነው::
እንግዲህ 'ጨለማ የለበሱ' የሚለው አኛንም የሚያጠቃልል ከሆነ —መንግስቱ ይህንን በመግለጫው
አለለየምና— መግለጫው የታቀደው ወደፊት ሊፈፀሙ የሚችሉትን ፀረዲሞክራሲያዊ ድርጊቶች ለመሸፈን
ነው ማለት ነው::

በሌላ በኩል:መንግስቱ እውነተኛ ተራማጆች የዚህ አይነቱን አድሃሪ ጽሁፍ ይበትናሉ ብሎ
ከገመተ፤ አሁንም ለነዚህ ነፃ ጋዜጦቻችን አደጋ አለ ማለት ነው::ይህ ነው እንዳይባል ደግሞ
በዚሁ መግለጫ ውስጥ መንግስቱ 'በመላው የኢትዮጵያ ተራማጆች የተደገፈው የመለዮ ለባሾች አላማ..
ወዘተ.' እያለ ጽፎአል::ይሁን እንጂ የዚህ አይነት አድሃሪ ስራ ከኢትዮጵያ ኮሙኒስቶችና ተራማ
ጆች ብእር ጨርሶ ሊመጣ እንደማይችል እምነቱ መሆኑን በግልጽ ማስፈር ነበረበት::
የዚህ አይነቱ መግለጫ በሚወጣበት ጊዜ በፍፁም አሻሚ መሆን የለበትም::በአሁኑ ሰአት
ለደርጉም:ለተራማጁም:ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ያለው ትልቅ አደጋ የኢምፔሪያሊዝም:የውስጥና
የውጭ አድሃሪዎች ተንኮል ነው እንጂ አንዳች ከግራ በኩል የሚሰነዘር 'የስልጣን ሽሚያ' ወይንም
ያንዳች'ቡድን እምነቱን በሕዝቡ ላይ' የመጫን አደጋ አይደለም::
ወታደራዊው መንግስት በተባለው የተንኮል ወረቀት ሳቢያ ከሰጠው መግለጫ ውስጥ አንዱ
ጥሩ ነጥብ ቢኖር የሚከተለው ነው:—

'የተማረውና የተደራጀው ወገን ለመሪነት በሰፊው ሕዝብ ይታጭ ዘንድ፣ አስቀድሞ ሰፊውን ሕዝብ ማስተማር ይኖርበታል::ሕዝብን ማስተማር ከሕዝብ መማርንም ይጠይቃል::...ወደሕዝቡ እንሂድ፣ እናስተምር፣ ከሕዝቡም እንማር::.....'

አባባሉ በጣም ጥሩ ነው::ግን ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበት ሁኔታ:ጋዜጦቻችንን እንኳን ባንገላመጥ ለማሰራጨት በማንችልበት ሁኔታ:እንዴት ሕዝቡን ለማስተማር ይቻላል? ሕዝቡስ በምን መንገድ ስሜቱንና ምኞቱን በመግለጽ ሊያስተምረን ይችላል? ማንም እንደሚያውቀው፣ ትምህርት የሚገኘው በነፃ ለመወያየትና ለመከራከር ሲቻል አይደለም?

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከተፈቀዱ አድሃሪያችም ይደራጃሉ፣ ያወናብዳሉ ይባላል::ታዲያ ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት 'በቂ ሃይልና ድርጅት' አለኝ ካለ፣ ዲሞክራቲካ የፖርቱጋል ወታደሮች ንቅናቄ እንደሚያደርገው ለምን በፀረሕዝብ መደቦችና ክፍሎች ላይ ተገቢ ቁጥጥር እያደረገ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በነፃ እንዲደራጁ አስፈላጊውን አካባቢ አይፈጥርም? እንደገና ለማስገንዘብ የምንፈልገው ኢምፔሪያሊዝምና ቡችሎቹ እስካሉ ድረስ የኢትዮጵያን ተራማጆች ለማስጠፍጨፍ፣ በኤኮኖሚ:በፖለቲካና ባስገባቸው ቀዳዳ ሁሉ እየገቡ ሳቦታዥ ለማድረግና በመጨረሻም አሁን በስልጣን ላይ ያለውን ደርግ ገልብጠው በቦታው አንዳች አድሃሪ ደርግን ወይም ሌላ የራባቸውን ምልምል መንግስት ለማቆም፣ አለያም ይህንኑ ደርግ ራሱን ቀስ በቀስ እያሻሹ የጥቅማቸው ጠባቂና ታዛዥ አሽከር ለማድረግ መፍጨርጨራቸው ፈጽሞ የማይቀር መሆኑን ነው::የወታደራዊው ደርግ ግራ ክንፍ በዚህ ነገር ላይ ካልነቃበት፣ እውነተኛ ጠላትንና እውነተኛ ወዳጅን ካላለየ፣ በነርሱ ወጥመድ ውስጥ ወድቆ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ሬቮሉሽናዊ ትግል ወደመቀልበስ ሊጋዝ ይችላል::ዛሬ ተራማጆቻችን የሚጠብቃቸው አንደኛው ከፍተኛ አደጋ ይህ ነው::

000000000000

## የነመለስ ተከሌ መገደል

አድሃሪያች በተረሸኑ ቁጥር ወታደራዊው መንግስት አንዳንድ ተራማጆችንም አብሮ የመረሸንን ፖለቲካ እንደልማድ የወሰደው ይመስላል::እነዚያ የታወቁ አድሃሪያች የዛሬ አራት ወር በተረሸኑበት ወቅት ተራማጆችም አብረው ተገድለው እንደነበር ይታወሳል::አሁንም ከሃይሉ ረጋሳና እነጌድ ጥላሁን ገዛውን አስገድሉአል ከሚባለው ከአሉላ በቀለ ጋር ሶስት ወጣት ተራማጆች አብረው ተረሸነዋል:: እነዚህ ሶስት ወጣቶች እንደተነገረው በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ፈጽመው እንደሆነ የመንግስቱ መግለጫ አያሳይም::እነዚያን ቦምቦች ለማፈንዳታቸው ምንም የቀረበ ማስረጃ የለም::እንዲያውም ሁለቱ በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ አንዳልነበሩ ይነገራል::ታዲያ የእነዚህ ወጣት ተራማጆች ንፁህ ደም የፈሰሰው ለምንድነው? ለፍርድ ሳይቀርቡ እንደቀረቡ አስመስሎ መነገሩስ ምን ጥቅም ሊያስገኝ ነው? ማንን ለማሞኘት ነው? መለስ ተከሌ:ግደይ ገብረዋህድና ረዘነ ኪዳኔ በተማሪው አካባቢ የታወቁ ተራማጆች ነበሩ::የእነዚህ ተራማጆች መገደል በቀላሉ የሚታለፍ ነገር አይደለም::የአንድ ንፁህ ተራማጅ መሞት የአድሃሪያችን እጅ ያጠነክራል፣ የሰፊውን ሕዝብ ትግል በመጠኑም ቢሆን ወደሃላ ይጎትታል::ስለዚህ ፋሽስታዊ ድርጊት ነው::

የነርሱ መገደል ለሁንም ቢሆን መንግስቱ እውነተኛ ወዳጁንና ጠላትን እንዳላለየ ያሳያል:: ይህም መንግስቱን እራሱን:በተለይም የደርጉን የግራ ክንፍ ለብቻው የሚነጥለውና መጥፊያውንም የሚያስከትል ድርጊት ነው::በርግጥ እነዚህ ወጣቶች ጥፋተኛ ናቸው ከተባለ ደግሞ ዝርዝር ሁኔታውን ግልጥልጥ አድርጎ ለሰፊው ሕዝብ ማቅረብ ያስፈልጋል::ያለበለዚያ፣ መንግስቱ ሺህ ጊዜ ደጋግሞ የሰፊው ሕዝብ ወገን ነኝ ቢልና ከሕዝብ የሚደብቅ ነገር የለኝም እያለ ቢለፍፍም ሰፊው ሕዝብም ሆነ ተራማጁ ክፍል ምንም አይነት እምነት ሊኖረው አይችልም::ውሎ አድሮም ከሰፊው ሕዝብና ከተራማጁ ወገን ይቆራረጣል፣ ታሪክም ይፋረደዋል::

እውነተኛ ወዳጆችና እውነተኛ ጠላቶች ይለዩ!
ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች!
ሰፊው ሕዝብ ያለራሱ ድርጅት ምንም አያገኝም!
ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ!
ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል!